# የእንቧይ ካቡን ትተን ለወደፊቱ የአለት መሰረት እናበጅ

በመርስኤ ኪዳን

ሰሞኑን የአንድነት ምክትል ሊቀመንበር የሆኑት ኢንጂነር ግዛቸው ሺፈራሁ “አንድነት ችግር ላይ ተጋርጧል . . . ሊዘጋ ይችላል” ሲሉ ዴይሊ ኔሽን ለሚባለው የኬኒያ ጋዜጣ መግለጻቸውን ሰንደቅ ጋዜጣ ታህሳስ 28 2002 ዓ.ም ባወጣው እትሙ አስፍሯል። የኢትዮጵያን ፖለቲካ በአንክሮ ለሚከታተል ሰው ይህ ዜና ብዙም አስገራሚ አይሆንበትም። ለምን ቢባል አንድነት መድረክ የተባለውን “የእንቧይ ካብ” የተቀላቀለ ጊዜ እንዳበቃለት ግልጽ ነውና። ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ የተነሳሳሁት የአንድነት ፓርቲ ለመፍረስ መቃረብ አሳስቦኝ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት የተሰባሰቡት የአንድነት አባላት በተለይም ወጣቶቹ የተሰባሰቡለት የኢትዮጵያ አንድነት ጉዳይ መድረክ በሚባለው ስብስብ ውስጥ ባሉ የጎሳ/የብሄር ፓርቲዎች ተጨናግፎ አንድነት የሚባለው ፓርቲም የአማራው ተወካይ መባሉ ስላልተዋጠልኝና የአንድነት ሀይሎች በጎሳ ፖለቲከኞች እየተሸነፉ መሄዳቸው እጅግ ስላሳሰበኝ ነው።

የ”አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ” አባላት በአንድነት ዙሪያ የተሰባሰቡት ለምንድነው?

የአንድነት አባላት በፓርቲው የተሰባሰቡት ቅንጅት በማኒፌስቶው ላይ ያሰፈራቸውን እሴቶች ይዘን እንታገላለን በሚል እንደሆነ የሚታወቅ ነው። የቅንጅት ማኒፌስቶ የመጀመሪያ አንቀጽ ቁጥር አምስት “የቅንጅት ልዩ ባህሪያት” የሚለው ክፍል ይህን አስፍሯል . . .

> *“ቅንጅት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የተለያየ ልምድ፣ አሠራርና ዝንባሌ ያላቸውን አራት <u>ሕብረ-ብሔር</u> ፓርቲዎች በማስተሳሰር ልዩነቶችን በውይይት፣ በድርድርና በመቻቻል ማስወገድ እንደሚቻል በተጨባጭ ያረጋገጠ የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ “*

እንግዲህ ከማኒፌስቶው የምንረዳው የቅንጅት ዋነኛ መለያ እሴት ህብረ ብሄራዊነት መሆኑን ነው። ከማኒፌስቶው በበለጠ ደግሞ መሪዎቹም ሆነ ደጋፊዎቹ ደጋግመው በኩራት “በዘር ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት”ላይ የተመሰረተ እንደሆነ ሲያስተጋቡ ቆይተዋል። የቅንጅት መንፈስ ወራሽ ነኝ የሚለው አንድነትም ለኢትዮጵያ አንድነት የሚሰራ ከጎሳ ፖለቲካ የጸዳ ፓርቲ እሆናለሁ ብሎ ነበር። ሆኖም ባልተጠበቀ ሁኔታ ኢህአዴግን በጎሳ የተደራጀ እያሉ ሲያብጠለጥሉ የነበሩ “ጊዜያዊ” የአንድነት መሪዎች በአገሪቱ አሉ ከሚባሉት ጎሰኞች ጋር መድረክ የተባለውን የእንቧይ ካብ በመቀላቀል የአንድነትን እሴት አሳንሰው ራሳቸውን የእንቧይ ካቡ ጫፍ ላይ ለማስቀመጥ ተሽቀዳደሙ።

ቅንጅት ቆሞላቸው የነበሩ የግለሰብ መብት፣ ህብረብሄራዊነት እና የመሳሰሉት እሴቶች ውሃ በላቸው። አሁን መድረክ ውስጥ ያለው ሁኔታ፣ ሊቀመንበር የምትለውን ስልጣን ላለማጣት መርሁን ጥሶ፣ እሴቱን አርክሶ የተቀላቀለ ሁሉ ሊቀመንበር፣ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር፣ የዚህ ሊቀመንበር፣ የዚያ ሊቀመንበር እየተባለ መሿሿም ሁኗል። እግዜር አያርገውና እኒህ ሰዎች ቢያሸንፉ

የስልጣን ፉክቻው ካሁኑ ይታየኛል። የኦሮሞ ፓርቲ መሪዎቹ “ወያኔ ትውደቅ” እንጂ የኦሮሞ ህዝብ “ማጆሪቲ” ስለሆነ ስልጣን ከኛ አትወጣም ብለው እርግጠኛ ሁነዋል፣ የቀድሞ የህወሓት አባላት ደግሞ እንደምንም እናሸንፍ እንጂ ጦር ሃይሉ ድሮም በኛ ይመራ ስለነበር መልሶ ለመቆጣጠር አይከብድም ጦር ሃይሉን ከተቆጣጠርን ደግሞ ሌላው አያስቸግርም ብለው ተዘጋጅተዋል፣ ሌሎቹ የጎሳ ፓርቲዎች ደግሞ በየክልሉ ስልጣን ለመቆናጠጥ ሽርጉዱን ተያይዘውታል። የአገሪቱን በጎሳ መከፋፈል በፍጹም አንቀበልም በሚሉ ኢትዮጵያውያን የተመሰረተው አንድነትፓርቲ ጥቂት መሪዎች ደግሞ የቅንጅት መንፈስ ከሚሉት መርሃቸው ጋር ፍጹም በማይጣጣም መልኩ ከጎሳ ፖለቲከኞች የሚወረወርላቸውን የስልጣን ፍርፋሪ ለመቀበል ተዘጋጅተዋል።

መራራ ጉዲናና ቡልቻ ደመቅሳ ቅንጅትም ሆነ ወራሽ ነኝ የሚለው አንድነት የአማራ ፓርቲ መሆኑን እንጂ በፍጹም በህብረብሄርነት እንደማይቀበሉት አቋማቸውን ግልጽ አድርገዋል። በቅርብ መድረክ እጩዎችን ለመጪው ምርጫ ለማደላደል ባደረገው ድርድር የመራራ ጉዲና ና የቡልቻ ደመቅሳው “ኦፌኮ” አንድነት ከአዲስአበባ፣ ከናዝሬትና ከድሬዳዋ ውጪ አንዲት የኦሮሚያ ወረዳ ላይ እጩ ማሰለፍ አይችልም የሚል ቁርጥ አቋም ይዘዋል። መራራ ጉዲና አንድነቶችን

> “እናንተ ኮ ነፍጠኞች ናችሁ፣ ህዝባችን ከነፍጠኞች ጋር ተባበራችሁ እያለ መከራችንን እያበላን ነው። እናንተን ተሸክሞ መዞሩ ለኛ አሳፋሪ ነው። የኦሮሚያን ጉዳይ ለኛ ተዉትና እናንተ አማራ ላይ አተኩሩ። አዲሳበባን ደግሞ እንካፈላለን።”

ብለው እቅጩን ነገሯቸው። የገብሩ አስራት “ዓረና” ደግሞ እኛ አዲሳበባንም አንፈልግም ምንም አንፈልግም ብቻ ትግራይ ላይ ድርሽ እንዳትሉብን ሲል አቋሙን አሳወቀ የሱማሌውም እንደዛ፣ የደቡብም እንደዛ። ታዲያ አንድነት ምን ቀረው? አማራ ክልልና ከፊል አዲስአበባ ብቻ! ታዲያ እንዲህ ከሆነ አንድነት የሚለው ስም ይገባዋል? . . . አይመስለኝም! ያው የኢህአዴጉ ኢህዴን ስሙን ወደ ብአዴን እንደቀየረው “አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲም” ስሙን “የአማራ ፌደራላዊ ኮንግረስ” ብሎ ቢቀይረው የሚሻል ይመስለኛል።

ይህን ጽሁፍ ለመጻፍ ስነሳሳ በመድረክ ዙሪያ የተሰባሰቡት ያረጁ ያፈጁ የቀድሞ ማርክሲስት የአሁን “ስልጣኒስት” ፖለቲከኞች አንብበውት አካሄዳቸውን ይመረምራሉ ወይም ያስተካክላሉ የሚል የዋህነት አጥቅቶኝ አይደለም። በበየነ ጴጥሮስና በመራራ ጉዲና የተመሩ ህብረቶች፣ ጥምረቶች፣ ቅንጅቶች . . . የት እንደደረሱ አይተናል። ምናልባትም ከዚህ የምርጫ ዘመን በኋላ በፖለቲካው ለመቀጠል እድሜያቸው በፍጥነት እያመለጣቸው ያሉት የስለሳዎቹ ማርክሲስት የአሁን “ስልጣኒስት” ፖለቲከኞች ከአሁን በኋላ ምንም አይነት የረባ ስራ ይሰራሉ ብየም ተስፋ አላደርግም። ሆኖም ግን በአንድነት ስር የተሰባሰቡ ወጣት ኢትዮጵያውያንና በእስር ቤት የምትገኘው መሪያቸው ያ የቆሙለት መርህ “የአንድነት መርህ፣ የህብረብሄራዊነት መርህ፣ የግለሰብ መብት መርህ . . .” ተጥሶ ፓርቲያቸው ለጥቂት ግለሰቦች ስልጣን ጥማት ሲባል ተጠልፎባቸዋል (“hijack” ተደርጎባቸዋል)። አንዳንዶቹ ወጣቶች በፕሮፌሰር መስፍን እየተመሩ የፓርቲያቸውን hijack መደረግ ለመቃወም ስላደረጉት እንቅስቃሴ የተጠየቁት ኢ/ር ግዛቸው ሲመልሱ “እነዚህ ሰዎች የሰሩት ሰራ በትንሹ ሰባት አመት ሊያስቀጣቸው ይገባ ነበር።” በማለት መንግስት ያን ለምን አላደረገም ብለው አማረዋል። እነግዛቸው ስልጣን ቢይዙ ወጣቶቹንም ሆነ ፕሮፌሰሩን ሰባት አመት ያስሯቸው ነበር ማለት ነው። ኢህአዴግ ማረን እንደሚያሰኙን ሳይታለም የተፈታ ነው።  የተወሰኑ

ወጣቶችና ፕሮፌሰሩ ፓርቲያቸውን ለማዳን ያደረጉት ጥረት ከሸፈባቸው። አብዛኞቹ ምን እንደሚያደርጉ ግራ ገብቷቸዋል፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ተስፋ ቆርጠው እጅና እግራቸውን አጣጥፈው ቁጭ ብለዋል።

እነሀ ወጣቶች ያች የሚያልሟት ከጎሰኝነት የጸዳች የዜጎች መብት የሚከበርባት ኢትዮጵያን ለመፍጠር የሚያደርጉት ጉዞ ጥቂት የስልሳዎቹ ፖለቲከኞች ባደረጉባቸው ሸፍጥ ምክኒያት ተጨናግፎ መቅረት አለበት? አይመስለኝም። ታዲያ ምን ይሻላል? በሚቀጥለው ጽሁፌ እመለስበታለሁ።

እስከዚያው ሰላም

መርስኤ ኪዳን mersea.kidan@gmail.com